## 2. የእግዚአብሔር መንግሥትና የወንጌል እውነት

### 2፡1. እግዚአብሔር በፍጥረት ሁሉ ላይ ንጉሥና ገዥ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በፍጥረት ሁሉ ላይ የበላይ ገዥ አድርጎ ይገልጸዋል።ይህም ማለት በሰማይ፣ በምድር ከምድርም በታች ያሉ ፍጥረታት በሙሉ **በእርሱ ተፈጥረዋል፣በእርሱ አገዛዝና መግቦት ስር ናቸው ማለት ነው**።መዝሙር 103:191 ዜና መዋዕል 29:11

### 2.2 በኢየሱስ የተሰበከው የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል

በኢየሱስ የተሰበከው የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ነው።ምክንያቱም የእግዚአብሔር አገዛዝ በሕዝቡ ልብ ውስጥ እንደሚመጣ ወይም እንደሚሆን የሚያበስር ስለሆነ።ማቴ 3:2፤ ማቴ 4:17 ማር 1:15 ማቴ 12:28

- **ዘመኑ**

**ተፈጸመ፡-** በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አገዛዙን ለማስተካከል አንድ ቀን መሲሑን (ክርስቶስን) እንደሚልክ ቃል ገባ።**ዘፍ 3፤15** ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፣ ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው ይህ የግዛት ዘመን መጀመሩን አበሰረ። ይህ ማለት መንግሥቱ የሩቅ የወደፊት ተስፋ ብቻ ሳይሆን እውን መሆኑ እየቀረበ ነበር ማለት ነው።

- **የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች፡-** **“መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች”** የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔር አገዛዙ፣ ኃይሉና ሥልጣኑ በኢየሱስ በኩል በአዲስ እና ወሳኝ በሆነ መንገድ ወደ ዓለም እየገባ ነበር ማለት ነው።
- የሚያመለክተውም ኢየሱስ **በትምህርቱ**፣ በተአምራቱ ፣ **በኃጢአትና በአጋንንት** ላይ ያለው ሥልጣን የእግዚአብሔር አገዛዝ ቀድሞውንም እንደነበረ እና ሰዎች የእግዚአብሔር ኃይል በእርሱ ውስጥ ሲሠራ ማየታቸው ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቅርባለች የሚለውን ያረጋገጠ መሆኑን

የሚያሳይ

ነው። **"እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእ ግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች"** ።"ማቴ12:28

- **ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ።** ምላሽ ይጠይቃል የእግዚአብሔር መንግሥት ከተቃ ረበ ሰዎች ገለልተኛ መሆን አይችሉም። ለዚያም ነው ኢየሱስ እና ከእሱ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን **ንስሐ እንዲገቡ ከኃጢአት ተመልሰው በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር በእምነት እንዲኖሩ** የጠራቸው.

"መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ"ማቴ 4:17

**ማጠቃለያ**:-

የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት የእርሱ አገዛዝ፣ ሥልጣን እና ንግሥና ማለት ነው በአሁኑ ጊ ዜ በአማኞች ልብ እና ሕይወት በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ በኩል እየሰራ ነው። ይህም የእግዚአብሔር መንግስት መሰረታውያን ከምንላችው ሁለተኛው ነጥብ ነው።በዚህ መርዳት መንግስቱን መቀብል እውነተኛ የወንጌል አማኝ ያደርጋል።እውነተኛ የወንጌል አማኞች ደግሞ የመንግስቱ ዜጎች ናቸው።